የDC የኗሪነት ማረጋገጫ ቅጽ –2020-21 የትምህርት አመት

እርስዎ የግዛቱ ኗሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ እና ስለዚህ እርስዎ ወይም ተማሪዎ በ DC (ዲሲ) የህዝብ ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ብቁ መሆናቹን ለማረጋገጥ **ይህን ቅጽ ይጠቀሙ**። ሁሉም ቅጾች እና ደጋፊ የኗሪነት ሰነዶች ለመዝጋቢው ትምህርት ቤት ተሰጥተዋል።

ደረጃ አንድ፣ እርስዎን በተሻለ የሚገልጽዎትን የኗሪነት ማረጋገጫ ይምረጡ።

የ DC ኗሪነትዎን የማረጋገጫ ዘዴዎች ዝርዝር በገጽ ሁለት ላይ ተመልክቷል። ከታች ያሉትን ክፍል 2 እና 3 ከሞሉ በኋላ **አንዱን ይምረጡ**። ከክፍያ ነጻ በ DC (ዲሲ) የህዝብ ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ብቁ ለሆን፣ 1) አስመዝጋቢው ሰው ተገቢው ሰነድ ያለው ወላጅ፣ አዋቂ ተማሪ፣ ወይም ሌላ የጸና ህጋዊ ሞግዚት፣ አሳዳጊ ወይም ሌላ ዋና ተንከባካቢ መሆን አለበት፣ 2) **አስመዝጋቢው ሰው በColumbia (ኮሎምቢያ) ግዛት <u>በአካል የሚኖር</u> መሆኑን አረጋግጧል**፣ እና 3) አስመዝጋቢው ሰው ኗሪነቱን የሚያረጋግጥ በህግ እና ደምቦች ላይ በተገለጹት መሰረት የጸና እና ተገቢ የሆነ ሰነድ አቅርቧል።

ደረጃ ሁለት፣ ስለተማሪው እና አስመዝጋቢው ሰው መረጃ ያቅርቡ።

የተማሪ የመጠርያ ስም፣	**የተማሪ የአያት ስም፣**	**የትውልድ ቀን፣**
የ 2020- 21 የትምህርት አመት ትምህርት ቤት ስም ፣		
አስመዝጋቢው ሰው > የመጠርያ ስም፣	**የአያት ስም፣**	

እኔ ነኝ፣ ☐ የተማሪው ህጋዊ ወላጅ/ሞግዚት/አሳዳጊ ☐ አዋቂ ተማሪ ☐ የተማሪው ሌላ ዋና ተንከባካቢ እና የተሞላ የ OPC ቅጽ ☐ አካለመጠን ያልደረሰ ወላጅ እና በመሀላ የተረጋገጠውን የጽሁፍ መግለጫ ሞልተዋል

የአስመዝጋቢው አድራሻ፣

ከተማ፣	**ክልል፣**	**ዚፕ፣**	**የDC ኗሪነት ፣** ☐ **አዎ** ☐ **አይደለም**
ኢሜይል፣		**ስልክ፣**	

ደረጃ ሶስት፣ የኗሪነት መስፈርቶችን ማረጋገጫ ይፈርሙ።

- እኔ ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ዋና ተንከባካቢ መሆኔን እና የጸና እና ተገቢ የኗሪነት ሰነድ እያቀረብኩ መሆኑን ወይም እኔ እራሴን ኗሪ አለመሆኔን መግለጼን አረጋግጣለሁ እና የሚያስፈልገውን የትምህርት ቤት የክፍያ ስምምነት እና ለምዝገባ የሚያስፈልገውን የትምህርት ቤት ክፍያን እረዳለሁ።
- እኔ በግዛቱ በአካል የምኖር መሆኑን ፣ ይህም "ቀጣይነት ላለው ክፍለጊዜ ለመኖር በማቀድ በእውነት የመኖርያ ቦታ በአካል መያዝ" ተብሎ ትርጉም ያለው ነው፣ እና እኔ በ5-A DCMR § 5004 ላይ በተገለጸው መሰረት ኗሪነቴን ለማረጋገጥ የጸና እና ተገቢ ሰነድ እያቀረብኩ ነው፣ ወይም፣ እኔ እራሴን ኗሪ እንዳልሆንኩ ገልጫለሁ እና የሚፈለገውን የትምህርት ቤት የክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ቤት ክፍያ አጠናቅቃለሁ።
- እኔ በመንግስት ድጋፍ የሚደረግለት የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም (Medicaid፣ TANF SNAP) ላይ ከተመዘገብኩ የግዛቱ ኗሪነቴን ለማረጋገጥ ብቻ የኗሪነትን መረጃየ እንዲገለጽ ፍቃድ እሰጣለሁ። ከታች በመፈረም ፣ እኔ ይህን እያልኩ ነው፣ እኔ በግል የሚለየኝን መረጃ የክልል የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education, OSSE) የDC ከሌላ ክልል ወይም የፌደራል ኤጀንሲዎች፣ የዲሲ የሰብዓዊ አገልግሎቶችን (Department of Human Services, DHS) ፣ የDC የመኖርያ ቤት ባለስልጣን (DC Housing Authority, DCHA) ፣ እና የጤና እንክብካቤ የፋያናንስ ዲፓርትመንት (Department of Health Care Finance, DHCF) እና ሌሎች ጨምሮ እንዲወስድ ፍቃድ ሰጥቻለሁ። OSSE መረጃየን ይጠብቃል እና የዚህን መረጃ ጥበቃ እና አጠቃቀም አስመልክቶ ሁሉንም አግባብ ያላቸውን ህጎች ይተገብራል።
- ከላይ ስሙ የተገለጸው ተማሪ በ ኮሎምቢያ ግዛት የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ወይም ሌሎች በ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኝ ትምህርታዊ አገልግሎቶች የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚመዘገበው እኔ **የሚታመን የቅን ልቦና የDC (ዲሲ) ኗሪን የምወክል ከሆነ፣ እና በአካል የምኖር መሆኑን በቃለመሀላ የተደገፈ መግለጫ እና ኗሪነቴን የሚያረጋግጥ የጸና እና ተገቢ የሆነ ሰነድ ካቀረብኩ** ወይም የትምህርት ቤት ክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ቤት ክፍያውን ከፈጸምኩ መሆኑን እረዳለሁ።
- የሰጠሁት መረጃ አጥጋቢ ቢመስልም፣ OSSE ወይም የትምህርት ቤት ሀላፊዎች፣ ምክንያታዊ መሰረት ካላቸው፣ የተማሪ ኗሪነትን ወይም ተማሪውን የሚያስመዘግብ አዋቂ ሌላ ዋና ተንከባካቢ ሁኔታ ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ሊፈልጉ እንደሚችሉ እረዳለሁ።
- የኮሎምቢያ ግዛት፣ በ OSSE አማካኝነት፣ እኔ ኗሪ አለመሆኔን ከወሰነ ወይም በ 5-A DCMR § 5007 መሰረት ፍቃድ የሌለው ኗሪ መሆኔን ከወሰነ፣ እኔ የተማሪውን ያለፈ ክፍያ ለመክፈል ሃላፊ መሆኔን ፣ እና ተማሪው ከትምርህርት ቤት እንዲለቅ ሊደረግ እንደሚችል እርዳለሁ።
- እኔ ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ ከሰጠሁ፣ ለወንጀል ምርመራ ለDC ጠቅላይ መርማሪ ቢሮ ወይም በሀሰተኛ አቤቱታዎች እና በDC ኮድ § 38-312 መሰረት ይህም ማንኛውም ሰው ከተማሪ የኗሪነት ማረጋገጫ ጋር በተያያዘ ለህዝብ ባለሟል እያወቀ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ከ $2,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ90 ቀናት በማይበልጥ እስራት፣ ሆኖም በመቀጮ እና በእስራት በሁለቱም ባንድ ላይ እንደማያስቀጣ በሚደነግገው አንቀጽ ክስ እንዲመሰረትብኝ ለዲሲ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ ሪፈር ልደረግ እንደምችል እረዳለሁ።
- የዚህ ቅጽ ሁሉም ደጋፊ ሰነዶች በትምህርት ቤቱ የሚያዙ እና ለOSSE ፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና ሲጠይቁ ሌሎች ኤጀንሲዎች እንዲሁም ለDC(ዲሲ) ጠቅላይ መርማሪ እና ለ(DC) ዲሲ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ እንደሚሰጥ እረዳለሁ።
- እኔ የኮሎምቢያ መንግስት በእጁ ያለውን ማንኛውንም ህጋዊ መንገዶች በመጠቀም የኔን መኖሪያ እንደሚያረጋግጥ እረዳለሁ እና እኔ የኗሪነት መረጃየ አግባብ ባላቸው የአካባቢው ባለስጣልናት ለማረጋገጫ እና/ወይም ለምርመራ እንዲገለጽ ፍቃዴን እሰጣለሁ።
- **እኔ ማንኛውንም የራሴን ወይም የተማሪውን የመኖርያ አድራሻ ለውጥ ከተቀየረበት ጊዜ አንስቶ በሶስት ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ለማሳወቅ ተስማምቻለሁ።**

አስመዝጋቢው ሰው እዚህ ይፈርም ፣ _____ **ቀን፣** _____

ደረጃ አራት ፣ ይህን የተሞላ ቅጽ እና የሚመለከታቸውን ሰነዶች ወደ ትምህርት ቤትዎ ያምጡ።

ለትምህርት ቤቱ ሀላፊ አገልግሎት ብቻ የሚከተለው ዘዴ የ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት ኗሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ውሏል። አንድ ዘዴ ይምረጡ።

እኔ የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች መመርመሬን እና ከላይ የቀረበው መረጃ በኔ እውቀት፣ መረጃ እና እምነት መሰረት እውነት መሆኑን፣ ይህ ባይሆን ግን ሀሰተኛ ነገር በመግለጽ ቅጣት የሚከተለኝ መሆኑን በማወቅ አረጋግጣለሁ። እኔ በተጨማሪ ሁሉም የዚህ ቅጽ ደጋፊ ሰነዶች በትምህርት ቤቱ የሚያዙ እና ሲጠይቁ ለ OSSE ፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና ሌሎች ኤጀንሲዎች፣ የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ መርማሪ ቢሮ እና የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ቢሮ እንደሚሰጥ አረጋግጣለሁ።

የትምህርት ቤት ሀላፊ ስም (ይጻፉ) ፣ _____ **ፊርማ፣** _____ **ቀን፣** _____

ዘዴ A፣ የትምህርት ቤቱ ባለሟል ያረጋገጠው
- ☐ OSSE የኗሪነት ተረጋግጧል (QLIK ወይም ASPEN)
- ☐ የቤት አልባነት ላያዘን ተረጋግጧል
- ☐ የDC ዋርድ

ዘዴ B፣ አንዱን ሰነድ ይምረጡ
- ☐ የክፍያ ሰነድ
- ☐ የDC መንግስት የገንዘብ እርዳታ
- ☐ የተረጋገጠ የDC የግብር Form-D40 (ቅጽ-D40)
- ☐ የሚሊታሪ የመኖርያ ቤት ትእዛዞች
- ☐ የኤምባሲ ደብዳቤ

ዘዴ B፣ ሁለት ሰነዶችን ይምረጡ
- ☐ የDC ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ
- ☐ DC የመንጃ ፍቃድ/ አሽከርካሪ ያልሆነ መታወቂያ
- ☐ የቤት ኪራይ ከክፍያ
- ☐ የአገልግሎት ደረሰኝ ከከፍያ

☐ **ዘዴ C፣** የቤት ውስጥ ጉብኝት

☐ **ኗሪ ያልሆነ**

አስመዝጋቢው ሰው፣ የእርስዎን የ DC ኗሪ ለማረጋገጥ ከሚከተሉት ዘዴዎች (A-C) አንዱን ይከተሉ።

A

በትምህርት ቤቱ ባለሟል አማካኝነት ማረጋገጥ። እርስዎ ቤት አልባነት ካጋጠምዎ፣ የግዛቱ ጥበቃ ውስጥ ከሆኑ፣ እና/ወይም የግዛቱ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራም ተሳታፊ ከሆኑ፣ እንደMedicaid፣ ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም፣ ወይም ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ – የእርስዎ ትምህርት ቤት የእርስዎን መረጃ ሊኖረው ይችላል። የትምህርት ቤት ባለሟል ወይም የትምህርት ቤቱ የቤት አልባ ላያዘን ጋር ያረጋግጡ።

በግብር እና ገቢ ቢሮ አማካኝነት ያረጋግጡ (OTR)። በድጋሚ የሚመዘገቡ ቤተሰቦች/ተማሪዎች ኗሪነታቸውን አብዛኛውን ጊዜ በ OTR የኗሪነት ማረጋገጫ ሂደት ተጠቅመው ማረጋገጥ ይችላሉ። አስመዝጋቢው ሰው በቀዳሚው የበጀት አመት ግብሮች በ(DC) ዲሲ የከፈለ መሆን እና የተማሪ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ያለው መሆን አለበት። ተማሪው በተመሳሳይ የአካባቢ ትምህርት ቤት ኤጀንሲ በድጋሚ የሚመዘገብ እና ከመዋእለህጻናት- 12 ድረስ የሚመዘገብ መሆን አለበት። ወደ ሲስተሙ በ ossedctax.com አማካኝነት ይግቡ። ስኬታማ ከሆኑ፣ ማረጋገጫዎ በትምህርት ቤቱ ለመረጋገጥ ዝግጁ ይሆናል።

B

ደጋፊ ሰነዶችን በማቅረብ ማረጋገጥ። *ሁለም* እቃዎች በ DC (ዲሲ) የኗሪ ማረጋገጫ ቅጽ ላይ እና የትምህርት ቤቱ የመመዝገቢያ ሰነዶች ላይ እንደተቀመጡት የአስመዝጋቢውን ስም ተመሳሳይ ስም እና አድራሻ ማካተት አለባቸው።

ከዚህ ዝርዝር ውስጥ ኗሪነትን ለማረጋገጥ አንድ ነገር ብቻ ይፈለጋል።

- ይህ ቅጽ በትምህርት ቤቱ ከታየ ጊዜ አንስቶ በ45 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የጸና **የክፍያ ሰነድ** ። ለዚህ አመት የ DC (ዲሲ) የግል ገቢ ግብር የተቀነሰበትን ብቻ ማካተት አለበት እና ለተቀናሽ የሌሎች የማናቸውንም ክልሎች ዝርዝር ማካተት የለበትም፣ መጠኑ ዜሮ ቢሆንም እንኳን። በተጨማሪም ላሁኑ የግብር አመት እና ያሁኑ የክፍያ ጊዜ ከዜሮ የሚበልጥ የ DC የግል ገቢ ግብር የተቀነሰበትን ማስየት አለበት።
- **ከ ኮሎምቢያ ግዛት መንግስት የተሰጠ ጊዜው ያለለፈበት ኦፊሺያል የገንዘብ እርዳታ ሰነድ፣** ባለፉት 12 ወራት ለተመዝጋቢው ሰው የተሰጠ እና ለትምህርት ቤቱ ሲቀርብ ወቅቱ ያላለፈበት፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF)፣ Medicaid ፣ የክልል የህጻን ጤና መድን ፕሮግራም (SCHIP) ፣ ተጨማሪ የዋስትና ገቢ፣ የመኖርያ ቤት እርዳታ ወይም ሌሎች ፕርግራሞች የሚያካትት።
- **የተረጋገጠ Form D40 (ቅጽ D40)** በ DC (ዲሲ) የግብር እና ገቢዎች ቢሮ የተሰጠ፣ ያሁኑ ወይም ደግሞ በጣም የቅርብ ጊዜ የግብር አመት የ DC ግብሮች የተከፈለበት ማረጋገጫ እና የዲሲ የግብር እና ገቢዎች ቢሮ ማህተም ያለው።
- **ያሁን ጊዜ የሚሊታሪ መኖርያ ትእዛዞች ወይም የሚሊታሪው አርማ ያለው ሰነድ፣** የስራ ልውውጥ መሆን አለበት እና በDC ውስጥ ልዩ አድራሻውን መግለጽ አለበት።
- **የኤምባሲ ደብዳቤ** ባለፉት 12 ወራት የተሰጠ። ኦፊሺያል የኤምባሲ ማህተም እና የኤምባሲው ሀላፊ ፊርማ ሊያካትት ይገባል፣ እና አስመዝጋቢው ሰው እና ተማሪው ወይም አዋቂ ተማሪው በሚመለከተው የ DC የትምህርት አመት ላይ በኤምባሲው ንብረት ውስጥ ያለ ወይም የሚኖር መሆኑን ማመልከት አለበት።

ወይም

ከዚህ ዝርዝር ውስጥ ኗሪነትን ለማረጋገጥ ሁለት ነገሮች ብቻ ይፈለጋል።

- **የ DC (ዲሲ) የሞተር ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ፍቃድ** ወይም ኦፊሺያል በመንግስት የተሰጠ አሽከርካሪ ላልሆነ የተሰጠ የጸና እና ጊዜው ያላለፈበት መታወቂያ።
- **የ DC ሞተር የተሽከርካሪ ምዝገባ** የጸና እና ጊዜው ያላለፈበት።
- **የቤት ኪራይ ስምምነት** የጸና እና ጊዜው ያላለፈበት **<u>የኪራይ ገንዘብ የተከፈለበት ሌላ የተለየ ማረጋገጫ ያለው</u>**፣ እንደ የክፍያ ደረሰኝ፣ የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣ ወይም የተመነዘረ ቼክ ቅጂ።
  የኪራይ ውሉ የሚጀምርበትን ጊዜ፣ ወርሃዊ የክፍያ መጠን፣ የአከራይ ስም ማካተት አለበት፣ እና በአስመዝጋቢው ሰው እና በአከራዩ የተፈረመ መሆን አለበት።
  የተለየ የክፍያ ማረጋገጫው ከትምህርት ቤቱ የምርመራ ጊዜ በፊት ወዲያውኑ ባሉት ሁለት ወራቶች መሆን አለበት እና በቤት ኪራዩ ላይ የተገለጸውን ወርሃዊ ኪራይ መጠን ጋር መጣጣም አለበት።
- ***የአገልግሎት ክፍያ (ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ እና የውሃ ደረሰኞች ብቻ ተቀባይነት አላቸው)*** **<u>ክፍያው የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ የተለየ ደረሰኝን</u>**፣ ለምሳሌ የተከፈለበት ሰነድ ፕሪንት፣ የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣ ወይም የተመነዘረ ቼክ ቅጂ።
  የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኙ ትምህርት ቤቱ ይህን ቅጽ ከሚመረምርበት ጊዜ ሁለት ወራት ቀደም ብሎ ላለው ጊዜ የተደረገ መሆን አለበት።
  የተለየ የክፍያ ማረጋገጫው ለተደረገው ክፍያ በተለይ መሆን አለበት። በጣም የተለመደው ነገር ሁለተኛው ደረሰኝ የመጀመርያውን ደረሰኝ ክፍያ የተፈጸመበት የሚያሳይ ሁለት ተከታታይ ደረሰኞችን ማቅረብ ነው። በተጨማሪም የብድር ክፍያ እና የመንግስት ኤጀንሲ የአንድን አገልግሎት ክፍያ መቀነሱን የሚገልጽ ደብዳቤም ተቀባይነት ያላቸው የክፍያ ማረጋገጫ ናቸው።

C

በቤት ውስጥ ጉብኝት ማረጋገጥ። እርስዎ ከላይ ባሉት አንዱ ዘዴዎች ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ስለቤት ውስጥ ጉብኝት ከትምህርት ቤቱ ሀላፊ ጋር ያውሩ።

ኗሪ ያልሆነ ተማሪ ሆኖ መመዝገብ

ኗሪ ያልሆኑ ተማሪዎች የግዛቱ የህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ መማር የሚችሉት በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ብቁ የሆኑ የ DC ተማሪዎች ከሌሉ፣ LEA ተማሪውን ለመመዝገብ ከተስማማ፣ ከክልል የትምህርት ቢሮ ዋና ተቆጣጣሪ ጋር የተደረገ ስምምነት ካለ፣ እና የመጀመርያ የትምህርት ክፍያ ከተደረገ ብቻ ነው። የትምህርት ክፍያ ስምምነት እና የትምህርት ክፍያ ለመሙላት፣ እባክዎ ኢሜይል ያድርጉ በ osse.residency@dc.gov ። ኗሪዎች ያልሆኑ በ District's Pre-K Enhancement and Expansion Funding Program (ግዛቱ የቅድመመዋእለ ህጻናት ማሳደጊያ ወይም የማስፋፋያ ድጋፍ ፕሮግራም) መሰረት ለምዝገባ ብቁ አይደሉም።

ተማሪ ለማስመዝገብ ብቁ የሆኑ ሰዎች።

- **ወላጅ** - የተፈጥሮ ወላጅ፣ የእንጀራ ወላጅ፣ ተማሪውን በማደጎ የማሳደግ ወይም የመቆጣጠር ስልጣን ያለው ወላጅ፣ የጋራ አሳዳጊን ጨምሮ።
- **ሞግዚት** - ስልጣን ባለው ፍርድቤት የተሾመ የተማሪ ሞግዚት ።
- **አሳዳጊ** - ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አሳዳጊነት የተሰጠው ሰው።
- **ሌላ ዋና ተንከባካቢ** - ከወላጅ ወይም በፍርድ ቤት ከተሾመ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ውጪ የሆነ ሌላ ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ ወይም አብሮት ለሚኖረው ተማሪ ቁጥጥር እና ድጋፍ የሚያደርጉ፣ እና ወላጆቸው፣ አሳዳጊያቸው፣ ወይም ሞግዚታቸው በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት የሚፈለገውን እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት የማይችሉ ናቸው።
- **አዋቂ ተማሪ** - እድሜው 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ፣ ወይም በጋብቻ ምክንያት፣ በህግ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ መሰረት ከወላጅ ቁጥጥር ነጻ የተደረገ ሰው ነው።